# መመርያ

## የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ

ተዛማጅ ምንጮች:- ACA, ACF, COB-RA, COG-RA, IGT-RA, IRB-RA, JFA-RA, JGA, JHC, JHC-RA, JHF-RA

ኃላፊነት የሚመለከተው ጽ/ቤት: Chief of Teaching, Learning, and Schools; Chief of Districtwide Services and Supports; Chief of Strategic Initiatives

## ማሸማቀቅ፣ ወከባ፣ ወይም ማስፈራራት

A. **ዓላማ**

ሁሉም ተማሪዎች ከጉልበተኝነት፣ ትንኮሳ ወይም ማስፈራራት ነፃ የመሆን መብት እንዳላቸው ለማረጋገጥ

በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ንብረት ውስጥ ጉልበተኝነትን፣ ትንኮሳ እና ማስፈራራትን ለመከላከል

ግንኙነት ላይ ያተኮረ፣ እንግዳ ተቀባይ፣ ምቹ የትምህርት ቤት አካባቢን፣ ለእያንዳንዱ ተማሪ አካዴሚያዊ እና ግላዊ እድገትን ለማስቀጠል ውጤታማ የአሰራር ሂደቶችን ማዕቀፍ ለመዘርጋት።

B. **ጉዳዩ**

ት/ቤቶች ከጉልበተኝነት ጥቃት፣ ከዛቻ ወይም ከማስፈራራት ፀድተው አመቺና ሠላማዊ የትምህርት አካባቢ እንዲሆኑ የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ቁርጠኛ ነው። ደካማን መበደል፣ ወከባ፣ ወይም ማስፈራራት ትምህርትን ያወዛግባል የአካዴሚ ክንውንን፣ ስሜታዊ ጤንነትን፣ እና የት/ቤትን አውድ አሉታዊ ተፅእኖ ያስከትልባቸዋል።

C. **ሁኔታ**

1. የኤሌክትሮኒክስ ቴክኖሎጂን በመጠቀም የሳይበር ጉልበተኝነትን፣ ትንኮሳን (ወሲባዊ ትንኮሳን ጨምሮ)፣ ማስፈራራት፣ አላስፈላጊ ሥራ በማሠራት መቅጣት፣ ወይም MCPS ንብረት ውስጥ ለማንኛውም ሰው የጥላቻ አድሎአዊ ድርጊቶችን ጨምሮ ይህም ትምህርት ቤቶችን ይጨምራል። በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ፋሲሊቲዎች፣ በ MCPS አውቶቡሶች፣ እና/ወይም ተማሪዎችን የሚያካትቱ በ MCPS የሚደገፉ እንቅስቃሴዎች በ MCPS ባለቤትነት የተያዙ ወይም የሚተዳደሩ መስኮች/ሜዳዎች ላይ

የቃል፣ የአካል ወይም የጽሁፍ (የኤሌክትሮኒክስ ጥቃትን ጨምሮ) በቦርዱ ፖሊሲ መሠረት የጉልበተኝነት ጥቃት በሁለንተናዊ መልኩ የተከለከለ ነው።

2. በዚህ መመሪያ ዓላማ እና በሜሪላንድ ህግ መሰረት ጉልበተኝነት፣ ትንኮሳ ወይም ማስፈራራት የተከለከለ ባህሪ ነው–

a) ሆን ተብሎ የሚደረግ መጥፎ ተግባር፣ የቃል፣ የአካል ወይም የጽሁፍ ባህሪ፣ ወይም በ MCPS ንብረት ላይ ሆን ተብሎ የሚደረግ ያልተገባ የኤሌክትሮኒክስ ግንኙነት፣ በትምህርት ቤቶች፣ MCPS በሚያስተዳድራቸው ግቢዎች፣በ MCPS አውቶቡሶች፣ ተቋም እና/ወይም የ MCPS ተማሪዎችን የሚያካትቱ እንቅስቃሴዎች ላይ፣ ወይም የትምህርት ቤቶችን ተግባራት በእጅጉ የሚያበላሹ ስነምግባሮችን ሁሉ ያካትታል፣ እና

b) በተማሪው የትምህርት ጥቅሞች፣ እድሎች ወይም አፈጻጸም ላይ፣ ወይም በተማሪው አካላዊ ወይም ስነ-ልቦናዊ ደህንነት ላይ ከፍተኛ ጣልቃ በመግባት ከጥላቻ የመነጨ የትምህርት አውድ መፍጠር፣ እና –

(1) በቦርድ ፖሊሲ ACA እንደተገለጸው አድሎ የሌለበት፣ ፍትሃዊነት እና የብቃት ባህል፣ በተጨባጭ ወይም በታሰበ ግላዊ ባህሪያት የሚነሳሳ

(2) ወሲባዊ አኳኋን፣ የተማሪ ወሲባዊ የሰውነት ክፍሎች የተጋለጠበት ወይም የግብረ-ሥጋ ግንኙነት ተግባር የሚያሳይ መግለጫዎች ወይም ምስሎችን ጨምሮ፣ ወይም

(3) ማስፈራራት ወይም ከባድ ማስፈራራት

(a) የሀፍረተ ሥጋ ሰውነት ክፍሎች፣ በሜሪላንድ የተብራራ ህግ ኮድ፣ የትምህርት አንቀፅ §7-424 የተገለጹት እርቃናቸውን የወሲብ ብልት አካባቢ፣ ቂጥ፣ ወይም የሴት የጡት ጫፍ ማለት ነው።

(b) ወሲባዊ ግንኙነት ማለት፡- "Annotated Code of Maryland, Education Article, §7-424" ላይ እንደተገለጸው በተመሣሣይ ጾታ ወይም በተቃራኒ ፆታዎች መካከል፣ ሀፍረተስጋ-ለሀፍረተስጋ፣ ሀፍረተስጋን - በአፍ ማድረግ፣ በሀፍረተ ስጋ ብልት በቂጥ ማድረግ፣ ወይም በአፍና-በቂጥ ፍትወተ ስጋ መፈጸምን የሚገልጽ ነዉ።

3. በዚህ መመሪያ ዓላማ እና በሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ዲፓርትመንት (MSDE) መመሪያ መሰረት፣በ MCPS ንብረት ውስጥ በጉልበተኞች (ሳይበር ጉልበተኝነትን ጨምሮ)፣ ትንኮሳ ማድረግ ወይም ማንኛዉንም ሰው ማስፈራራት የሚያስከትላቸውን ጉዳቶች ለመቅረፍ የሚከተሉት ትርጓሜዎች በተግባር ላይ ይውላሉ፡-

a) ጉልበተኝነት ማለት በክፍል C.2 ውስጥ የተከለከሉ የስነምግባር መስፈርቶችን የሚያሟሉ እና በተማሪዎች መካከል የማይፈለግ፣ ወራዳ ባህሪ ማለት ሲሆን የሚከተሉትንም ያካትታል –

(1) የሃይል አለመመጣጠን (ጉልበተኞች አካላዊ፣ ስሜታዊ፣ ማህበራዊ ወይም አካዳሚያዊ ሀይላቸውን ተጠቅመው ሌሎችን ለመቆጣጠር፣ ለማግለል ወይም ለመጉዳት መጠቀም) እና

(2) መደጋገም (ከአንድ ጊዜ በላይ የተከሰቱ የጉልበተኝነት ባህሪያት ወይም በሚሰበሰቡ መረጃዎች ሊረጋገጡ የሚችሉ የመደጋገም ዕድላቸው ከፍተኛ የሆነ ጉልበተኝነትን ማሳየት)።

b) የሳይበር ጥቃት ማለት ሰክሽን C.2 እና C.3.a ላይ እንደተገለጸው የተከለከሉ የስነምግባር መስፈርቶችን የሚያሟላ እና በተንቀሳቃሽ የመገናኛ መሳሪያ አማካኝነት ግለሰቦች እንዲመለከቱት ወይም እንዲያሠራጩ የሚደረግ በኤሌክትሮኒክስ ግንኙነት የሚተላለፍ ጥቃት መሠንዘር ነው።

(1) የሳይበር ጥቃት ስለ አንድ ሰው ውርደትን የሚያስከትል የግል ገመና ወይም ግላዊ መረጃን ማሠራጨት፣ መለጠፍ ወይም ማዳረስን ያጠቃልላል።

(2) በትምህርት ቤት መቼት የሳይበር ጥቃት ከተፈጸመ የዲሲፕሊን እርምጃ ሊወሰድ ይችላል። ትምህርት የሚሰጠው በአካል ወይም ቨርቹወል ቢሆንም በትምህርት ቤት የሚገኙ ተማሪዎች ላይ የጉዳት አደጋን ይፈጥራል፣ ወይም የትምህርት አሰጣጥ ሁኔታን ያውካል።

c) የኤሌክትሮኒክስ ግንኙነት ስልክ፣ ኮምፒውተር፣ ወይም ተንቀሳቃሽ የመገናኛ መሣሪያን ጨምሮ በኤሌክትሮኒክ መሣሪያ የሚተላለፍ ግንኙነት ነው።

d) ጥቃት (የፆታ፥ የዘር ወዘተ) ወይም ትንኮሳ፡- section C.2 ላይ የተከለከሉትን የስነምግባር መስፈርቶች የሚያሟሉ ትክክለኛ ወይም በይሆናል ግምት የሚፈፀሙ አሉታዊ ድርጊቶች እና የአንድን ግለሰብ የግል ባህሪያት በተመለከተ ሌላውን ግለሰብ ማሰናከል፣ መሳለቂያ ማድረግ ወይም ማንቋሸሽ አድሎ የሌለበት፣ እኩልነት እና የብቃት ባህል፣ ወይም ወሲባዊ ባህርይ ሲሆን፣ በቦርድ ፖሊሲ ACF ላይ እንደተገለፀው፣ የተማሪዎች የፆታ ብልግና እና ጾታዊ ትንኮሳ፣ ወይም የቦርድ ፖሊሲ ACI ላይ እንደተብራራው፣ የሰራተኞች ወሲባዊ ትንኮሳ፣ የተማሪ ወሲባዊ የሰውነት ክፍሎች የተጋለጠበት ወይም የግብረ-ሥጋ ግንኙነት ድርጊትን የሚያጋልጥ መግለጫዎችን ወይም ምስሎችን መጠቀምን ይጨምራል።

e) ማስፈራራት፡- በክፍል C.2 የተከለከሉ ድርጊቶችን መስፈርት የሚያሟሉ እና የፍርሃት እና/ወይም የበታችነት ስሜትን የሚያስከትል በሌላ ግለሰብ ላይ የሚፈፀም ማንኛውም ግንኙነት ወይም ድርጊት ነው። የበቀል እርምጃ እንደ ማስፈራራት ሊቆጠር ይችላል።

4. ቦርዱ የጉልበተኝነት ትንኮሳን ወይም የማስፈራራት ድርጊቶችን ሪፖርት በሚያደርጉ ግለሰቦች ላይ ማናቸውንም የበቀል እርምጃ ለመከላከል ቁርጠኛ ነው። በጉልበተኝነት፣ ትንኮሳ ወይም ማስፈራራት ተጎድተዋል የተባሉ ተማሪዎችን፤ ወይም ምስክሮችን፣ ተመልካቾችን፣ ወይም ሌሎች ስለ ጉልበተኝነት ጥቃት፣ ትንኮሳ ወይም የማስፈራራት ድርጊት አስተማማኝ መረጃ ያላቸው ግለሰቦችን ከበቀል እርምጃ ለመታደግ ቁርጠኛ ነው።

5. በዚህ መመሪያ ውስጥ እንደተገለፀው በአካል የሚፈፀም ጉልበተኝነት (መምታት፣ መግፋት፣ መጎተት) የመሣሰሉትን የሚያካትት ሲሆን ነገር ግን በዚህ ብቻ አይወሰንም። የቃል (መሳለቅ፣ ማስፈራራት፣ ማስገደድ፣ ማሾፍ፣ የስም ማጥፋት)፣ ወይም ተዛማጅ የሆኑ (ወሬዎችን ማሰራጨት፣ ብቸኛ ማድረግ ወይም ማግለል) የመሣሰሉትን ይጨምራል።

D. **የአተገባበር ስልቶች**

1. ጉልበተኝነትን፣ ትንኮሳን፣ ወይም ማስፈራራትን እንዲሁም የጉልበተኝነት ማስፈራሪያ ድርጊቶችን በሚዘግቡ ግለሰቦች ላይ የሚደርሰውን የበቀል እርምጃ ለመከላከል ከተማሪዎች፣ ከአስተዳደር እና ከትምህርት ቤት ሰራተኞች ጋር በጋራ የመከላከል እና የጣልቃገብነት ስልጠናን የሚያካትት ስርአት አቀፍ ጥረት ይጠይቃል። ኢላማ የተደረገባቸው ግለሰቦች (ከዚህ በኋላ “ቅሬታ አቅራቢዎች” እየተባሉ የሚገለጹ) እና ሌሎችን አስፈራርተዋል፣ ወከባ ወይም ማስፈራራት ፈፅመዋል ተብለው የተከሰሱት (ከዚህ በኋላ “ተከሳሾች” እየተባለ የሚጠራው) ከፍተኛ የጤና፣ የደህንነት እና የትምህርት አደጋዎች ሊያጋጥማቸው ይችላል።

2. MCPS የሳይበር ጥቃትን፣ ትንኮሳን፣ ወይም ማስፈራራትን ጨምሮ የጉልበተኝነት ጥቃትን ስለመለየት እና ሪፖርት ስለማድረግ ለሰራተኞች እና ለተማሪዎች እንዲሁም ለበጎ ፈቃደኞች

ስልጠና ይሰጣል። ጉልበተኝነት፣ ትንኮሳ፣ ወይም ማስፈራራት ሲከሰት ጣልቃ ለመግባት፣ የጣልቃ ገብነት ስልቶችን ለመተግበር፣ እና አስፈላጊ ከሆነ የውጭ ሪፈራል ለመስጠት እንዲችሉ ውጤታማ መሆናቸው የተረጋገጡ የመከላከያ መርሃ ግብሮችን ተግባራዊ ለማድረግ ሰራተኞች በተገቢው ሁኔታ መዘጋጀት አለባቸው። በትምህርት ቤቶች ውስጥ ጉልበተኝነት፣ትንኮሳ ወይም ማስፈራራትን ለመከላከል እና የጥቃት፣ የማስፈራራት ወይም የዛቻ መዘዞችን በማስወገድ የማስተካከያ እርምጃዎችን ሪፖርት በሚያደርጉ ግለሰቦች ላይ የበቀል እርምጃ እንዳይወሰድ መከላከል የስርአቱ የመከላከል እና የጣልቃ ገብነት ፕሮግራም አካል መሆን አለበት። የዚህ ፕሮግራም አካላት የሚከተሉትን ማካተት አለባቸው:

3. ሙያዊ ትምህርት

ግንዛቤን ለማዳበር በማስረጃ ላይ የተመሰረቱ ልምዶችን በመጠቀም ለአስተዳዳሪዎች እና ለሰራተኞች አመታዊ ሙያዊ ትምህርት መስጠት-

a) የጉልበተኝነት፣ ትንኮሳ ወይም ማስፈራራት መስፋፋት መንስኤዎች እና ውጤቶች፤

b) በተለይም በምሳ ሠዓት፣ የእረፍት ጊዜ፣ እና መተላለፊያ መንገዶች ላይ፣ ተማሪዎች እቃዎቻቸውን በሚያስቀምጡባቸው የመቆለፊያ ክፍሎች በመሳሰሉ ቦታዎች ከትምህርት ክፍል ውጪ በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች የአዋቂዎች መገኘትና መቃኘት አስፈላጊነት፣

c) የትምህርት ቤትን ድባብ ለማሻሻል እና ጉልበተኝነትን፣ ትንኮሳን ወይም ማስፈራራትን ለመቀነስ ሁለገብ፣ የተሃድሶ አቀራረብን መጠቀም፣

d) ደህንነቱ የተጠበቀ፣ ምቹ፣ በምላሽ ሰጭ ባህል የዳበረ የትምህርት ቤት እና የመማርያ ክፍል ልምምዶች፣ ማህበራዊ/ስሜታዊ ትምህርትን ማቀናጀት፣ በአሰቃቂ ሁኔታ የተለከፉ ልምድ ያላቸውን፣ እና ሁሉንም ተማሪዎች ምቾት እንዲሰማቸው፣ አካታች እና እንዲገናኙ የሚያግዝ የተሃድሶ አቀራረቦችን መተግበር፣

e) ግንዛቤን እና ችሎታን የማዳበር ስትራቴጂዎች-
   (1) ዒላማ በተደረገባቸው ተማሪዎች፣ የጥቃቱ ተከላካዮች እና ተመልካቾች ላይ ጉልበተኝነት፣ትንኮሳ እና የማስፈራሪያ ባህሪያት ያላቸውን ተፅእኖ መረዳት እና መለየት እና ተገቢውን ምላሽ መስጠት፣

   (2) ጉልበተኝነትን፣ ትንኮሳን፣ ወይም ማስፈራራትን እና የሚያስከትሏቸውን ውጤቶች ለመከላከል እና የማስተካከያ እርምጃዎችን ለመውሰድ በጥናት ላይ የተመሰረቱ ስልቶችን መጠቀም፣

(3) በቦርድ ፖሊሲ ACA ላይ በተገለጹት ጉልበተኝነት፣ ትንኮሳ ወይም ማስፈራራት ተጋላጭ ለሆኑት በተጨባጭ ወይም በይሆናል ግምት የግል ባህርይ ላይ በመመስረት ለተማሪዎች የድጋፍ እርምጃዎችን መስጠት

4. መከላከል እና ትምህርት

MCPS በሁሉም ትምህርት ቤቶች ውስጥ አወንታዊ፣ሠላም ያለው እና የሚያበረታታ የት/ቤት ድባብ መኀልበት ላይ አጽንዖት በመስጠት ተማሪዎች አካላዊ እና ስሜታዊ ደህንነት እንዲሰማቸው በሁሉም ትምህርት ቤቶች ውስጥ የአዎንታዊ ባህሪ ድጋፎች እና የትምህርት ቤት አውድን የማሻሻል ጥረቶችን ለማረጋገጥ በየትምህርት ቤቱ በማስረጃ ላይ የተመሰረቱ ትምህርታዊ ፕሮግራሞችን ይሰጣል።

a) ለሁሉም ተማሪዎች ሁለንተናዊ የጤና ትምህርት መስጠት፡ ይኼውም በሰዎች መካከል ስላለው ግንኙነት እና ስለ ጉልበተኝነት ጥቃት፣ የሳይበር ጥቃት፣ ትንኮሳ፣ ማስፈራራት እና የጉልበተኝነት ጥቃት ሪፖርት ቅጽን ያካትታል።

b) ለወላጆች፣ ለበጎ ፈቃደኞች እና ለሰፊው ማህበረሰብ ልጆቻቸውን ለመደገፍ የሚያስችሏቸውን ስልቶች፦ ስለ ጉልበተኝነት ጥቃት፣ ስለ ትንኮሳ እና ማስፈራራት የመስፋፋት መንስኤ እና መዘዝ ግንዛቤ እንዲያዳብሩ እድሎችን መስጠት፤ የማህበረሰብ ደህንነት ጠንቅ ሊሆን የሚችል የጉልበተኝነት ጥቃት፣ ትንኮሳ ወይም ማስፈራራትን በሚመለከት የማስፈራራትን ምልክቶች ስለማወቅ እና ሪፖርት ማድረግ ግንዛቤ ማስጨበጥ፣

c) በጉልበት ማጥቃት፣ትንኮሳ፣ ወይም ማስፈራራት የህዝብ ጤና ጠንቅ እንደሆነ ለማሳወቅ እና ለቅሬታ አቅራቢዎች፣ ምላሽ ሰጪዎች እና ተመልካቾች የጤና አጠባበቅ ሪሶርሶች መኖራቸውን እንዲያውቁ ለመርዳት ከማህበረሰብ ጤና ጥበቃ እና ከአእምሮ ጤንነት ሪሶርሶች ጋር መሥራት፣ እና

d) የተማሪዎችን በጉልበተኝነት ጥቃት፣ትንኮሳ ወይም ማስፈራራት የመከላከል ጥረቶችን ጨምሮ፣ የቅሬታ ሰሚዎችን እና ምላሽ ሰጪዎችን ደህንነት በማረጋገጥ ጉልበተኝነትን፣ ትንኮሳን ወይም ማስፈራራትን ለመከላከል የተለያዩ የባህሪ ጣልቃገብነቶች፣ እና የደህንነት ዕቅዶች ተዘጋጅተዋል። ለጉልበተኝነት፣ ለትንኮሳ ወይም ለማስፈራራት ኢላማ ተደርገው የተጋለጡ እኩዮችን ድጋፍ በመስጠት የሚያበረታቱ የጋራ መከባበር እና ልዩነትን እና ባህልን የማህበራዊ ስሜትን የሚያበረታቱ ፕሮግራሞች ይኖራሉ።

5. የማሸማቀቅ፣ ወከባ፣ ወይም የማስፈራራት ተግባሮች ሪፖርት አቀራረብ ቅደም-ተከተሎች

a) MCPS የጉልበተኝነት፣ ትንኮሳ ወይም የማስፈራሪያ ድርጊቶችን ለማሳወቅ ምቹ፣ ደህንነቱ የተጠበቀ፣ የግል እና ከእድሜ ጋር ተመጣጣኝ የሆኑ አሠራሮችን ለትምህርት ቤቶች ይሰጣል።

b) ተማሪዎች፣ ሰራተኞች እና ወላጆች/አሳዳጊዎች MCPS ቅጽ 230-35፣ ጉልበተኝነት፣ ትንኮሳ፣ ወይም ማስፈራሪያ ሪፖርት ማቅረቢያ ቅጽ መኖሩን እና በእያንዳንዱ ትምህርት ቤት ስለ ሪፖርት አቀራረብ ሂደቶች ይነገራቸዋል።

(1) በ MCPS ስለ ማሸማቀቅ፣ ወከባ፣ ወይም የማስፈራራት ተግባሮችን ሪፖርት ማድረግ የሚበረታታ እና የሚደገፍ ተግባር ነው። ሪፖርት ማድረግ ለቅሬታ አቅራቢዎች፣ ምላሽ ሰጪዎች እና በምስክርነት ለተመለከቱት እርዳታ እንደሚደርስላቸው MCPS ግልጽ መልእክት ያስተላልፋል።

(2) ርእሰመምህሩ/ዳይሬክተሩ ወይም ተወካዩ አግባብነት ባለው የመግባቢያ ሠነድ እና የ MCPS ደንብ COB-RA፣ አደጋና አስቸኳይ ክስተት ሪፖርት ስለማድረግ ባለው ድንጋጌ መሠረት ስለተፈጠሩት ክስተቶች ወዲያውኑ የህግ አስከባሪ አካላትን ማነጋገር አለባቸው።

(3) በሜሪላንድ ህግ መሰረት፣ አንድ የትምህርት ቤት ሰራተኛ የጥቃት፣ ትንኮሳ ወይም ማስፈራሪያ ድርጊት ሪፖርት ሲያደርግ/ስታደርግ ባልተሟላ ሁኔታ በማድረጉ(ጓ) ምክንያት ወይም ባለማሳወቁ(ቋ) በህግ ተጠያቂ አይሆንም/አትሆንም።

6. ስለማሸማቀቅ፣ ወከባ፣ ወይም ማስፈራራት ፈጣን ምርመራ የማካሄድ ቅደም-ተከተሎች

a) ርእሰ መምህሩ/ተወካዩ ስለ ጉልበተኝነት፣ትንኮሳ ወይም ማስፈራሪያ ሪፖርቶች ማስረጃዎችን ለማቅረብ የክስተቱን አጋጣሚ ጨምሮ አግባብነት ባለው ህግ መሰረት በቂ፣ አስተማማኝ እና ገለልተኛ ምርመራ ወዲያውኑ ማካሄድ አለበት።

b) ምርመራውን ሲያጠናቅቅ ርእሰ መምህሩ/ተወካዩ የሚያስከትለውን መዘዝ ለማስወገድ በቅሬታ አቅራቢው ማስፈራራት፣ ማሸማቀቅ፣ ዛቻ ወይም ወከባ፣ ትንኮሳው እንዳይደገም ለመከላከል እንደአግባቡ አስፈላጊ እርምጃዎችን ይወስዳል።

c) ርእሰ መምህሩ/ተወካዩ በህግ አስከባሪ አካላት ካልተመራ በስተቀር በ 48 ሰአታት ውስጥ በጉልበተኝነት ጥቃት፣ ትንኮሳ ወይም ማስፈራሪያ ሪፖርት ተለይተው የታወቁትን ተማሪዎች ወላጅ/አሳዳጊ ያነጋግራል።

d) ምርመራው ካለቀ በኋላ፣ ጉልበተኛው፣ ትንኮሳው ወይም ማስፈራሪያው እንደቀጠለ ለማወቅ የሰራተኞች አባላት ከቅሬታ አቅራቢው እና ከተጠሪ ጋር በግል ስብሰባ ያካሂዳሉ።

7. የሚያስከትሏቸው መዘዞችና የመፍትሄ እርምጃዎች

ሌሎችን ለጎዱ ሰዎች የባህሪ ጣልቃገብነት ስልቶች እና የማስተካከያ እርምጃዎች፣ ወይም በበቀል ለተሳተፉ ሰዎች፣የሀሰት ውንጀላ ላደረጉ፣ ትንኮሳ ወይም ማስፈራራት የፈጸሙ ሰዎች በቦርድ ፖሊሲ ACA፣ አድሎ የሌለበት፣ ፍትሃዊ እና የብቃት ባህል መሰረት በፍትሃዊነት እና በሚዛናዊነት ይተገበራሉ። የቦርድ ፖሊሲ JGA፣ የባህሪ ጣልቃገብነት ሠላም እና ደህንነት እቅድ፣ እና MCPS ደንብ JFA-RA፣ የተማሪ መብቶች እና ሀላፊነቶች።

8. ለቅሬታ አቅራቢዎች፣ ምላሽ ሰጪዎች እና ታዳሚዎች የጣልቃ ገብነት እና የድጋፍ አገልግሎቶች ይሰጣሉ።

a) MCPS ለሁለቱም ቅሬታ አቅራቢዎች እና ምላሽ ሰጭዎች ፈጣን ምላሽ ሰጭ ማህበራዊ/ስሜታዊ ድጋፎችን ያዘጋጃል፣ ይህም ከአሰቃቂ ሁኔታ የማገገም እና የተሃድሶ አቀራረብ ይሆናል። እነዚህ ተጋላጭ ሊሆኑ ለሚችሉ ተማሪዎች እና የማስፈራሪት፣ የትንኮሳ፣ ወይም የዛቻ ባህሪ ላላቸው ተማሪዎች እንዲሁም ለቅሬታ አቅራቢዎች እና ምላሽ ሰጪዎች በግለሰብ ደረጃ ጠንካራ ድጋፎችን ሊያካትት ይችላል።

b) እንደአግባቡ፣ የቅሬታ አቅራቢዎች እና ምላሽ ሰጪዎችን የመቋቋም አቅም ለመገንባት፣ ማህበራዊ ግንኙነቶችን እና የአቻ ግንኙነቶችን ለማዳበር፣ ተጨማሪ የጉልበተኝነት ጥቃት ክስተቶች የሚፈጠሩባቸውን አጋጣሚዎች ለመቀነስ እና የተማሪን የደህንነት ስሜት እና ማህበራዊ ግንኙነት ለማሳደግ ድጋፎች ሊሰጡ ይችላሉ።

c) አንድ የማሸማቀቅ፣ ወከባ፣ ወይም ማስፈራራት አድራጎትን በማስመልከት ከሥራ ባልደረባ ጋር ለመወያየት አንድ ተማሪ ፍላጎት ካለው/ካላት፣ ሠራተኛው(ዋ) የተማሪው(ዋ)ን ጥያቄ ስራ ላይ ለማዋል በማያስቸግር፣ ደህና/አስተማማኝ፣ ግላዊ፣ እና ከእድሜ-ጋር-አግባብ ባለው መንገድ ለመተግበር ጥረት ያደርጋል/ታደርጋለች።

d) MCPS በትምህርት ቤቶች እና በማህበረሰቡ ውስጥ ለቅሬታ አቅራቢዎች፣ ምላሽ ሰጭዎች እና ሁኔታውን የተመለከቱ ግለሰቦች የተለያዩ የምክር እና የአእምሮ ጤና ድጋፎችን ለተማሪዎች እና ለቤተሰቦች ይሰጣል።

9. የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት በ MCPS ውስጥ ያለውን የሪፖርት ማቅረቢያ እና የምርመራ ሂደቶችን የሚያውቅ የ MSDE ሰራተኛ ስም እና አድራሻ የሚገልጽ ይህንን ፖሊሲ ተግባራዊ ለማድረግ ደንቦችን ያወጣል። እንደአስፈላጊነቱ ለወላጆች/አሳዳጊዎች እና ለህግ አስከባሪ አካላት የጥቃት፣ ትንኮሳ ወይም ማስፈራሪያ ክስተቶችን ሪፖርት የማድረግ እና የመመርመር ሂደቶች፤ ለቅሬታ አቅራቢዎች፣ ምላሽ ሰጪዎች እና ሁኔታውን የተመለከቱ ሰዎች የድጋፍ እርምጃዎች፣ መዘዞች ወይም የማስተካከያ እርምጃዎች፣ እና ሂደቶቹን የማስታወቅ አሠራር እና ክስተቶች ላይ ክትትል የሚደደረግበትን ሁኔታ ያካትታል።

10. የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ይህንን ፖሊሲ ተግባራዊ ለማድረግ እና በትምህርት ቤቶች ውስጥ የጉልበተኝነት ጥቃትን፣ ትንኮሳን ወይም ማስፈራራትን ለመከላከል ለተማሪዎች እና ለሰራተኞች ትምህርታዊ እና ሙያዊ እንቅስቃሴዎችን ያዘጋጃል።

11. በቦርድ-የፀደቁ መመርያዎችን በመደገፍ የዳበሩ ደንቦችን እንዲያውቁት ለቦርዱ ይላካሉ።

E. ተፈላጊ ውጤት

ትምህርት ቤቶች ከጉልበተኝነት ጥቃት (ሳይበር ጥቃትን ጨምሮ)፣ ከትንኮሳ እና ከማስፈራራት የፀዳ የትምህርት አካባቢ ለመፍጠር የመከላከል፣ የባህሪ ጣልቃገብነት፣ ሥላም እና ደህንነት ስትራቴጂዎችን እንዲሁም ያስከተለውን መዘዝ ለመቅረፍ ደጋፊ እርምጃዎች ይወሰዳሉ።

F. ግምገማ እና ሪፖርት

ይህ ደንብ በቦርድ ድህረ እይታ ሂደት ይገመገማል።

**ተዛማጅ ምንጮች:** Annotated Code of Maryland, Education Article, §7-303.1, §7-424, §7-424.1; Code of Maryland Regulations 13A.08.01.15; Maryland State Department of Education Maryland's Model Policy to Address Bullying, Harassment, or Intimidation 2021 Update; A Student's Guide to Rights and Responsibilities in MCPS; Student Code of Conduct in MCPS; Guidelines for Respecting Religious Diversity; Guidelines for Student Gender Identity

**የፖሊሲው ታሪክ፡** የውሳኔ ቁጥር 132-10፣ ማርች 9፣ 2010 የፀደቀ አዲስ መመሪያ፤ ኖቬምበር 15, 2016 በውሳኔ ቁጥር 489-16 የተሻሻለ የቴክኒካዊ ማሻሻያዎች በውሳኔ ቁጥር. 319-17፣ ጁን 26/2017፤ ቴክኒካል ማሻሻያ በውሳኔ ቁጥር 351-18 ጁን 25 ቀን 2018; በውሳኔ ቁጥር 113-22፣ ማርች 8፣ 2022 ተሻሽሏል።